# *Case Reports*

## Note

The following reports are cases decided by the Cassation Division of the Federal Supreme Court of Ethiopia. The purpose of publishing the cases is to make them known to the members of the legal profession. The case reports in a single issue of the *Journal* bring together interesting decisions on a give area of law. For this issue judgments on the subject matter of Family Law are chosen.

In selecting a particular judgment for publication the Editorial Committee do not want to imply that the judgment is definitive on any proposition or that it contains erroneous propositions. The cases are chosen for the interesting issue(s) of law they raise.

የሰ/መ/ቁ. 3477
መጋቢት 9 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ሐጎስ ወልዱ
4. ወ/ት ሒሩት መለሠ
5. አቶ ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ሰይድ ይመር - ጠበቃ ማስረሻ በላይ

ተጠሪ፡- የአማራ ክልል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አልቀረበም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ በጊዜው ሥራ ላይ በነበረውና በአዋጅ ቁጥር 214/74 ተሻሽሎ በወጣው የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 23/1/ /ሀ/ እና /ለ/ ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመጥቀስ 3 /ሶስት/ የወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡

የተጠሪ ክስ ለአመልካች ደርሶም ባቀረበው የመቃወሚያ ክርክር ተከሣሽ የተጠቀሰውን የወንጀል ድርጌት ፈጸመ ከተባለ በኋላ አዲስ የወንጀል ሕግ የወጣ እንደመሆኑ መጠን ይህም አዲስ የወንጀል ሕግ ተከሣሽን የሚጠቅም ስለሆነ መከሰስ የሚገባኝ በአዲሱ የወንጀል ሕግ እንጂ በቀድሞው ሊሆን ስለማይችል ክሱ ተሻሽሎ ሊቀርብ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ተጠሪም በበኩሉ ከአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5/1 አኳያ ክርክሩ መቀጠል የሚገባው በተሻረው ሕግ መሠረት ስለሆነ ክሱ ሊሻሻል ስለማይገባ መቃወሚያው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ተከሣሽ ድርጊቱን ፈጸመ በተባለበት ጊዜ የነበረው ሕግ ተሽሮ አዲስ የወንጀል ሕግ የወጣ ሲሆን በተሻረው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሙስና ወንጀል ተብሎ የተቀመጠው ድርጊት ተሽሮ በአዲሱ የወንጀል ሕግ የሙስና ወንጀል ተብሎ ከአንቀጽ 407 ጀምሮ የተደነገገ ከመሆኑም በላይ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ላይ የተደነገገው ቅጣት ከተሻረው ሕግ ቅጣት ያነሰና ተከሳሽን የሚጠቅም እንደሆነ በብይኑ ላየ አስፍሮ አዲሱ የወንጀል ሕግ ተከሳሽን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ ስለሚችል ከሳሽ በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 407/1/ ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ ክሱን አሻሽሎ እንዲያቀርብ ይህ ድንጋጌም የዋስትና መብት ስለማይከለክል ተከሣሽ የብር 5000/አምስት ሺህ/ ዋስትና ሲያሟላ በዋስ ሆኖ ክርክሩን እንዲቀጥል በማለት ብይን ሠጥቷል፡፡

የሥር ከሣሽ የአሁን ተጠሪ በዚሁ ብይን ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ጠቅላየ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የወንጀል ሕግ ተከሳሹን የሚጠቅም ከሆነ ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም ነገር ግን ተፈፃሚነት የሚኖረው በጥፋተኛነትና በቅጣት ጊዜ ስለመሆኑ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 6 ላይ የተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የክርክሩ ሂደት ሳይጠናቀቅ ክሱ እንዲሻሻል በማዘዝ ዋስትና መፍቀዱ በአግባቡ አይደለም በማለት የሥር

ፍ/ቤትን ብይን በመሻር መ/ሰጭው /የአሁን አመልካች/ ጉዳዩን በማረሚያ ቤት ሆኖ ሊቀጥል ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለወንጀል ሕግ ቁጥር 6 የሰጠው ትርጉም ተጠሪ ባለበት ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የዋስትና መብት ሊፈቀድለት ይገባል? ወይንስ አይገባም? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ በመያዝ አቤቱታዉ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ወንጀል ፈጽሟል የተባለው አዲሱ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት መሆኑ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ወንጀሉ የተፈጸመው አዲሱ የወንጀል ሕግ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ከሆነ ተከሣሹ መከሰስ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 5 መሠረት በአዲሱ ሕግ ሳይሆን ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ ሥራ ላይ በነበረው ሕግ መሠረት ነው፡፡

በሌላ በኩልም ተከሣሽ የሚከሰሰው በቀድሞው ሕግ መሠረት ቢሆንም የቀድሞው የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአዲሱ የወንጀል ሕግ ተሽሮ የሙስና ወንጀሎችንም በተመለከተ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 407 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 437/97 መሠረትም በተከሣሹ ላይ ሊወሰን የሚችለው ቅጣት ከ10 ዓመት በታች ከሆነ የዋስትና መብት ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

አመልካች የወንጀሉን ድርጊት ፈጽሟል በተባለ ጊዜ የነበረው ሕግ የተሻረ ቢሆንም መከሰስ የሚገባው ድርጊቱ በተፈጸመ ጊዜ ሥራ ላይ በነበረውና አመልካችም በሚያውቀው ሕግ መሠረት መሆን እንደሚገባው ከሕግ መርህ /Rule of legality/ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመርህ ደረጃ የተሻረ ሕግ ተፈፃሚነት ባይኖረውም ወንጀሉ ተፈጸመ በተባለ ጊዜ ተከሣሹ የሚያውቀው ይህንኑ የተሻረ ሕግ ስለሆነ ክስ መቅረብም የሚገባው ይሄው የተሻረ ሕግ ተጠቅሶ ነው፡፡ ይህም የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ /exception to the general rule/ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአዲሱ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 5 ላይም የተንጸባረቀው ይህንኑ መሠረት አድርጎ ነው፡፡

አመልካች መከሰስ የሚገባው በቀድሞው ሕግ መሠረት ከሆነ ጥፋተኛም የሚሆነው በዚሁ የቀድሞ ሕግ መሠረት መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ በሌላ በኩልም የወንጀል ሕግ በመርህ ደረጃ ወደ ኋላ ተመልሶ እንደማይሰራ ነገር ግን ተከሣሽን የሚጠቅም እስከሆነ ድረስ ወደ ኋላ ተመልሶ ሊሰራ እንደሚችል በአዲሱ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 6 ላይ እና በህገመንግስታችን አንቀጽ 22 ላይ ተመልክቷል፡፡

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል ሕግ ቁጥር 6 ላይ የተመለከተውና የወንጀል ሕግ ተከሣሹን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሶ ይሰራል ተብሎ የተደነገገው ተፈፃሚነቱ በቅጣት ጊዜ እንጂ ክርክሩ በተጀመረበት ደረጃ ተፈፃሚነት ስለማይኖረው የዋስትናው ጉዳይ መታየት ያለበት ከተከሰሰበት ድንጋጌ አኳያ በመሆኑ የተከሰሰበትም ድንጋጌ የዋስትና መብት ስለማይፈቅድ አመልካቹ በእሥር ሆኖ ሊከራከር ይገባል ብሏል፡፡

በመርህ ደረጃ የተሻረ ሕር ተፈፃሚነት የሌለው ሲሆን በተሻረ ሕግ ክስ ማቅረብ ደግሞ የመርሁ ልዩ ሁኔታ ነው፡፡ የተሻረውም ሕግ ተጠቅሶ በተከሳሹ ላይ ክስ የሚቀርበው ወንጀሉ ተሰርቷል በተባለ ጊዜ ሕጉ ሥራ ላይ ስለነበርና ተከሣሹም ያውቀዋል ተብሎ ስለሚገመትና በሚያውቀው ሕግ መሠረት መከራከር እንዳለበት የሕግ መርህ /Rule of legality/ ስለሚያስገድድ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የተሻረው ሕግ የሚጠቀሰው ተከሳሹ ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት እንዲያስችለው እንጂ ከዚህ ያለፈ ውጤት የሌለውና መጨረሻም ላይ ቅጣት የሚወሰነው ሥራ ላይ ባለ ሕግ ላይ ተመስርቶ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህም ሌላ የዋስትና ጉዳይ በዋናነት የሚታየው ቅጣትን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ አመልካች የተከሰሰው የዋስትና መብት በሚከለክል ድንጋጌ ቢሆንም ድንጋጌው የሚጠቀሰው ክርክሩን በአግባቡ ለመምራት ታስቦ እንደሆነ ሕጉ ይዞት የተነሳውን ዓላማ መገንዘብ ከተቻለ የዋስትናው ጉዳይ መታየት የሚገባው ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አኳያ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡

ክርክሩ እልባት ካገኘ በኋላ አመልካች የሚቀጣው በአዲሱ ሕግ መሠረት እንደሆነ ከወዲሁ በግልጽ መገንዘብ እየተቻለ ክርክሩ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በእሥር ይቆይ ማለት ሕግ አውጭው የዋስትና መብት ሊከለክላቸው ያልፈለገውን ተከሣሶች የዋስትና መብት እንደመከልከል የሚቆጠርና ሕጉም የታለመለትን ዓላማና ግብ እንዳይመታ የሚያደርግ ነው፡ ፡

ስለሆነም በአመልካች ላይ ቅጣት ሊወሰንበት የሚችለው በአዲሱ የወንጀል ሕግ በቁጥር 407/1/ ሥር ስለሚሆንና በተሻሻለው የጸረ ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 437/97 መሠረት ከ10 ዓመት በታች በሚያስቀጡ የሙስና ወንጀሎች የዋስትና መብት የተፈቀደ ስለሆነ አመልካችም ሊቀጣ የሚችለው ከ10 ዓመት በታች ስለሆነ የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሱ እንዲሻሻል ትዕዛዝ መስጠቱ አግባብነት ባይኖረውም የዋስትና መብት መፍቀዱ ግን ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ብይን በመሻር ለአመልካች የዋስትና መብት ሊፈቀድለት አይገባም በማለት የሰጠው ፍርድ ከላይ ከተመለከተው አኳያ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 285/99 ጥቅምት 4 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 14168 በ9/6/99 ዓ.ም. ለአመልካች የዋስትና መብት በመፍቀድ የሰጠው ብይን በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለአመልካች ዋስትና በፈቀደው መሠረት ዋስትናውን እንዲያሟላ በማድረግ አመልካች በዋስ እንዲከራከር ታዟል፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 53612

ሚያዝያ 25 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. ሒሩት መለሠ
2. ተሻገር ገ/ስላሴ
3. ታፈሰ ይርጋ
4. አልማው ወሌ
5. ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- 1ኛ. አቶ ፍሰሐ ዓባይ
2ኛ. ወ/ሪት ህይወት የስራው } ጠበቃ አቶ ሰለሞን ደምሴ

ተጠሪ፡- የገቢዎችና ጉምሩክ ዓ/ሕግ አቶ ገ/እግዛብሔር ሙናቸው ቀረቡ፡፡
መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን ፍርድ ሰጥረናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾች ላይ በቀረበው የወንጀል ክስ ጉዳይ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ አመልካቾች ቅር ተሰኝተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩም አመጣጥ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡ የገቢዎችና ጉምሩክ አቃቤ ሕግ በአመልካቾች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እና እንደተሻሻለው አንቀጽ 22/1/ እና መ/ለ/1/ ላይ የተመለከተውን በመተላፍ ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ፈጽመዋል የሚል ሲሆን፣ አመልካቾች ይህንኑ የወንጀል ድርጊት አልፈፀምንም በማለት ከደው በመከራከራቸው ክርክር ቀጥሎ ሁለቱም ወገኖች በየፊናቸው ማስረጃ አቅርበው አሰምተዋል፡፡

የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በኮ/መ/ቁ. 144285 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ሁለተኛ አመልካች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ስለመፈጸሟ የተረጋገጠ ሲሆን፣ አንደኛ አመልካች የንግድ ድርጅቱ ባለቤት እንደመሆናቸው ግብይት ያለደረሰኝ እንዳይከናወን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው በሠራተኛ ለተፈፀመው ድርጊት ኃላፊነት አለባቸው በማለት በሁለቱም ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ካገናዘበ በኋላ 1ኛ ተከሳሽ በብር 20,000.00(ሃያ ሺ ብር) እና በ1(አንድ) ዓመት እስራት ሁለተኛ አመልካች በብር 10,000.00(ሙቶ ሺ) ብር እና በ1(አንድ) ዓመት እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

በዚህ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ አመልካቾች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ ማቅረባቸው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ተመልክቶ የአሁን አንደኛ አመልካች በተፈፀመው ድርጊት ቀጥተኛ ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ ስላልተረጋገጠ በነፃ ይሰናበታል በማለት ሲወስን፤ ከጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔ ግልባጭ ላይ መረጃት እንደሚቻለው የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ የተሰጠው የእስራት ቅጣት አንሷል በማለት አቅርቦት የነበረው የይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ በጥፋተኝነትም ሆነ በቅጣት ረገድ በሰጠው ውሳኔ የገቢዎችና ጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ ሁለተኛ የይግባኝ አቤቱታ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በማቅርቡ፤ የጠቅላይ የፍ/ቤቱ ሁለቱም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ በወ/ይ/መ/ቁ. 51336 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በጥፋተኝነት ውሳኔ አሰጣጥ በኩል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ አመልካች ላይ የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ከፀና በኋላ በቅጣት አጣጣል ረገድ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት ድንጋጌ ሥር ከተመለከተው ዝቅተኛ የቅጣት መነሻ በታች ለመውረድ የሚያበቃ ህጋዊ ምክንያት አልተገኘም በማለት የገንዘብ መቀጮውን ሳይነካ ሁለቱም አመልካቾች እያንዳንዳቸው በሁለት ዓመት እስራት እንዲቀጡ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከዚህ በላይ በተመለከተው አኳኋን የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ዝርዝር ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ለዚህም የሰበር ቅሬታ ተጠሪ የገቢዎችና ጉምሩክ አቃቤ ሕግ መልስ እንዲሰጥበት ተደረጐ በሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1ኛ. አመልካች ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ተፈጽሟል በተባለበት ጊዜ በተፈፀመው አድራጐት ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ በማስረጃ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ የአንደኛ አመልካች የጥፋተኝነት መሰረት ሆኖ የተያዘው በአድራጐቱ የተነሣ የተፈፀመው ጥፋት ሳይሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/1/ እንደተመለከተው ድርጅቱ አዋጁን በመተላፉ ስለፈፀመው ጥፋት ተተክቶ ተጠያቂ ሊሆን በመቻሉ ነው በዚህ መሰረት ከተጠያቂነት ለመዳን የሚቻለው በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 56/3/ የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ በጠቅላይ ፍ/ቤት የውሳኔ ሐተታ እንደተመለከተው ይህ ስለመሆኑ አንደኛ አመልካች ሕጉ የጣለበትን ግምት ለማስተባበል የሚያስችል የመከላከያ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 56/1/ "…አንድ ድርጅት…." የሚለውን አባባል ከአንቀጽ 56/4/ ድንጋጌ ሥራ አስኪያጅ የሚለው አባባል ለየትኞቹ ድርጅት የሚለውን ጥያቄ ሊያስነሳ እንደሚችል የተረዳን ቢሆንም በአዋጁ መግቢያ "ትርጓሜ" ለሚለው አንቀጽ 2/5/ እና 2/11/ ጋር አገናዝበን ስንመለከተው ድርጅት ማለት በሽርክና ማህበር በኩባንያ እና በሰዎች ህብረት ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ አይታይም፡፡

ሁለተኛ አመልካችንም ቢሆን ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ቦታ ተገኝታ ከፈፀመችው ካደረገችው እና ከተናገረችው አድራጎት አንፃር በድርጊቱ አፈፃፀም ቀጥተኛ ተሳትፎ ስለመሆኑ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በዚህ ሁሉ ምክንያት በሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔን አስመልክቶ የተሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የጠቅላይ ፍ/ቤት በተጠሪ ይባኝ መነሻ በአመልካቾች ላይ ተጥሎ የነበረውን የአንድ ዓመት እስራት ወደ ሁለት ዓመት እስራት ለውጦ በማሻሻል ሊወስን የቻለው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 82/1/ሀ/ ከተመለከተው ዝርዝር የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አንዱ የሆነው የጥፋተኛው የዘወትር ጠባይ መልካም መሆን ብቻውን እንደ ቅጣት ማቅለያ ሊወሰድ አይችልም፡፡ የዘወትር ጠባዩ መልካም መሆን ብቻ ሳይሆን ያጠፋውም በእውቀት ማነስ፣ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም ባልታሰበና ድንገተኛ አጋጣሚ

እንደሆነ ጭምር መሆን ይገባዋል፡፡ በዚሁ ድንጋጌ የዘወትር ጠባይኑና የአፈፃፀሙን ሁኔታም "እና" በሚለው ምህፃሂረ ቃል መያያዙ ሁለቱም ሁኔታዎች ድርብ የቅጣት ማቅለያ ማሚያ ምክንያቶች መሆናቸውን አመልካች ነው የሚለውን በመያዝ እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል፡፡

ይሁን እንጂ ቅጣትን የማቅለልና ከቅጣት ነፃ የማድረግ ደንብን አስመልክቶ በተመለከተው የሕግ ክፍል በወ/ሕ/ቁ. 179 ላይ "ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሰረት ቅጣትን ማለቅለል እንደሚችል በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ......" ለሚለው አነጋገር "በሕግ በተደነገገ ጊዜ ሁሉ...." የሚለው ሐረግ ስለቅጣት ማቅለል በወ/ሕ/ቁ. 82/1/ሀ/ የተመለከተው ድንጋጌ ብቻ ሳይሆን ከቅጣት አወሳሰን ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስለቅጣት አጣጣል አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አጣቅሶ ማየት እንደሚያስፈልግ አመላካች ነው፡፡

ከዚህም አኳያ በወ/ሕግ ቁጥር 88/2/ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ያለፈ የሕይወት ታሪክ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ መደንገጉ አንድ አጥፊ ወንጀሉን እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የዘወትር ጠባዩ መልካም የነበረ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ለቅጣት ማቅለያነት የማይወሰድበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህም ሁሉ ታልፎ በወንጀል ሕግ ቁጥር 82/1/ሀ/ የተመለከተው የቅጣት ማቅለያ ወጥነት ያለው የተጣመረ ምክንያት ነው እንኳ ቢባል በሥር ፍ/ቤቶች የቅጣትን አስተያየት አስመልክቶ በግራ ቀኙ በየደረጃው ከተደረጉት ክርክሮች፣ ከድርጊቱ አፈፃፀም ወንጀሉን ላቋቋመው ድንጋጌ ወይም ሕግ ጋር ሁሉ ተገናዝቦ ሲታይ በዚህ አከራካሪ በሆነው ድንጋጌ "እና" ከሚለው ቀጥሎ ካሉት ወይም በሚል ምሕጻረ ቃል ከተያያዙት አንዱን ምክንያት ቢሆን እንኳ አመልካቾች አላሟሉም ማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም የተነሣ ቅጣቱ በመደበኛ የቅጣት ማቅለያ ደንብ መሰረት ማውረድ አይገባም የሚለውን ታሳቢ በማድረግ አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉት ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን መነሻ የሁለት ዓመት እስራት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መጣሉ/መወሰኑ የቅጣት አጣጣል ሥርአትን የተከተለ ሆኖ አላገኘውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በቅጣት አወሳሰን ረገድ ላይ ብቻ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 51336 የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡ በዚህ ረገድ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 144285 ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም. የጣለው ቅጣት ፀንቷል፡፡
2. አመልካቾች የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ እንደተገለፀው አንደኛ አመልካች በብር 20,000.00(ሃያ ሺህ ብር) እና በአንድ ዓመት፣ ሁለተኛ አመልካች በብር 10,000.00(አስር ሺህ ብር) እና በአንድ ዓመት እስራት ይቀጣሉ በማለት በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195/2/ለ/2/ መሰረት አሻሽለን ወስነናል፡፡ ለፌዴራል ማ/ቤቶች ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች
ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 35697
ሚያዝያ 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. ዓብዱልቃድር መሐመድ
2. ሒሩት መለሠ
3. ታፈሰ ይርጋ
4. አሊ መሐመድ
5. ሱልጣን አባተማሞ

አመልካች፡- የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ - ዓቃቢ ሕግ አውግቸው መኮንን ቀረበ፡፡
ተጠሪ፡- ከበደ ወርቅነህ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ኀዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ታህሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ የምዕራብ ጎጃም ዞን ዓቃቤ ሕግ በከሣሽነት ተጠሪ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ በየዞኑ ዓቃቤ ሕግ በተጠሪ ላይ፣ መጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም. ከምሽቱ በግምት አራት ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት በማቃጠል በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተኝተው የነበሩት ይታይሽ አለማየሁ፣ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያው በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ ያደረገ በመሆኑና ድርጊቱን የፈፀመው በእሳት ቃጠሎ ምክንያት በውስጥ ያሉ ሰዎች ሊሞቱ እንደሚችሉ እያወቀ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ 539/1/ሀ/ በመተላለፍ የሆነው ይሁን በሚል ተነሳስቶ በመሆኑ ከባድ የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፤ ይህ የሚታለፍ ቢሆን በአማራጭ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/2/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ፈጽሟል፤ እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 494 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን በመተላለፍ ግምቱ ከብር 20000.00/ሃያ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ንብረት ሙሉ በሙሉ እንዲወድም አድርጓል የሚሉ ክሶችን አቅርቦበታል፡፡

ተጠሪ ዓቃቢ ሕግ ባቀረበው ክስ የገለፃቸውን የወንጀል ድርጊቶች አልፈፀምኩም በማለት ክዶ በመከራከሩ ዓቃቤ ሕግ ሁለት ምስክሮች አሰምቷል፡፡ ተጠሪ ለወረዳ ፍርድ ቤት በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠውን የዕምነት ቃል በሰነድ ማስረጃነት አቅርቧል፡፡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቤቱ ከውጭ እንደተቆለፈ በእሳት የተቀጣጠለ መሆኑንና በክሱ ስማቸው የተገለፀው ሰዎች በእሳት ተቃጥለው መሞታቸው ልዩነት በሌለው ሁኔታ የመሰከሩ መሆኑንና ሁለተኛው የዓቃቤ ህግ ምስክር በእሳት ተቃጥላ የሞተችው ሴት ተከሣሽ መኩሪያው ተጋፋውን ከነቤተሰቦቹ ቆልፌ በእሳት አቃጥላለሁ እያለ ይዝት እንደነበር ከዚያ ቀን በፊት ነግራናለች በማለት የመሰከረ መሆኑን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ያሣያል፡፡

ሌላው በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ በወንጀለኛ መቀጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 መሠረት የሰጠው የዕምነት ቃል ሲሆን መጋቢት 29 ቀን 1998 ሌሊት 4 ሰዓት ሲሆን የመኩሪያው ተጋፋውን ቤት አቃጥየዋለሁ፤ ያቃጠልኩት መጋቢት መባቻ ላይ በዱላ ስለመታኝ ነው፤ ቤቱ ከውጭ ተቆልፎ የነበረ በመሆኑና

የቤቱ ባለቤት ወደ ማህበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ ነው ያቃጠልኩት፤ ቤቱም ከውጪ ተቆልፎ ነበር የሚል ይዘት የለው ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ተጠሪ በወቅቱ በአካባቢው ያልነበረ መሆኑን ሁለት የመከላከያ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543/3/ የተመለከተውን በመተላለፍ በቸልተኝነት ሶስት ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ነው፤ እንደዚሁም በወንጀል ሕጉ 691 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣቱን በተመለከተ ለመጀመሪያው ጥፋት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ፣ በሁለተኛው ጥፋት በሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና በአምስት መቶ ብር መቀጮ በጥቅሉ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራትና በሁለት ሺህ ብር የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በእሳት ተቃጥለው የሞቱትን ሰዎች በተመለከተ ተጠሪ ሊያደርገው የሚችለው ጥንቃቄ አልነበረም፤ የሀሣብ ሁኔታው አልተሟላም በማለት ሙሉ በሙሉ በነፃ እንዲለቀቅ የወሰነ ሲሆን የሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና አምስ መቶ ብር ቅጣት በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት አለበት፤ ተጠሪ ቤቱን በማቃጠል የግል ተበዳይ ያደረሰበትን ጉዳት ለመበቀል አስቦ ያደረገው መሆኑ በሰው ምስክርም ሆነ በጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፤ ተጠሪ ከምሽቱ አራት ሰዓት በመሄድ ቤት ያቃጠለው ንብረት ለማውደም ብቻ ሣይሆን ሰዎች የሚተኙበት በእንቅልፍ ሰዓት በመሆኑ የግል ተበዳይን ከነቤተሰቡ በእሳት ለማቃጠል በነበረው ሀሣብ እንደሆነ በማስረጃ አስረድተናል፤ ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአማራጭ የቀረበውን በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል ተጠሪን ጥፋተኛ ሲል ዓቃቤ ሕግ ይግባኝ ያልጠየቀ በመሆኑ በከባድ ሰው መግደል ተጠሪ መጠየቅ አለበት ብለን ለመከራከር የሥነ ሥርዓት ገደብ ቢኖርብንም ከዚህ አልፎ የጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል ቸልተኝነት የለም በማለት መወሰኑ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 እና 543/3/ የተዛባ ትርጉም የሰጠና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሰራ መሆኑን ስለሚያሣይ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ መልስ ይዞ እንዲቀርብ መጥሪያ የደረሰው ሲሆን መልሱን ይዞ አልቀረበም፡፡ ስለሆነም በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ከሥር የክርክሩ አመጣጥና የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ ቤቱን ከምሽቱ አራት ሰዓት ያቃጠለው ከግል ተበዳይ መኩሪያው ተጋፋው ጋር ከዚያ ፊት ተጣልተው የግል ተበዳይ በዱላ ስለደበደበው መሆኑን የዓቃቤ ሕግ የሰነድ ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የግል ተበዳይን ቤት ከውጭ ቆልፌ ከነቤተሰቡ ነው የማቃጥለው በማለት ይዝት እንደነበር አንደኛዋ ሟች ነግራኛለች በማለት አስረድቷል፡፡

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱ መመዘን አለበት በማለት የሰጠው ትችት ተቀባይነት ያለው የማስረጃ አመዛዘን መርህ በመሆኑ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ከነሙሉ ይዘቱና መልዕክቱ የመዘነ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ዓቃቤ ሕግ የጽሁፍ ማስረጃ አድርጎ ባቀረበው የተጠሪ ዕምነት ቃል የግል ተበዳይ ወደ ማህበር ሲሄድ ስላየሁት ቤተሰቦቹም ሄደዋል ብዬ በማሰብ ቤቱን አቃጠልኩት የሚል ፍሬ ጉዳይ አለ፡፡

ከዚህም የምንረዳው ተጠሪ በእሳት ቃጠሎ ሕይወታቸው ያለፈው የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ወደ ማህበር ሲሄዱ ያላያቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ሟቾች ወደ ማህበር ስለመሄዳቸው እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ማህበር ሂደዋል ብሎ ስለገመተ ብቻ ቸልተኝነት የለበትም ለማለት አይቻልም፡፡ ወቅቱ ሌሊት ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግል ተበዳይን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው ከቤት ሊኖር እንደሚችል ማወቅ ሲገባው ወይም እያወቀ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 59 የተደነገገውን ቸልተኝነት የሚያሟላ ነው፡፡ የሟቾች ከቤታቸው ውስጥ ተኝተው መገኘት ከተጠሪው አቅም በላይ የሆነ ኃይል ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈፀመ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ጥፋተኛ ነው በማለት የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረበው ማስረጃ ተጠሪ ከግል ተበዳዩ ጋር በነበረው ጠብ በቂም በቀል ተነሳስቶ የግል ተቀዳይን ቤት በእሳት ያቃጠለ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ተጠሪ በለኮሰው እሳት ተቃጥለው ሰዎች ሞተዋል፡፡ ተጠሪ ቤቱን የማቃጠል እንጂ ሟቾቱን የመግደል ሀሣብ አልነበረውም ቢባል እንኳን በቸልተኝነት ሟቾችን በመግደሉ ተጠያቂ የማይሆንበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ሊያደርገው የሚገባው ጥንቃቄ አልነበረም፡ በቸልተኝነት በሰው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለበትም በማለት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13840 ኅዳር 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ተጠሪ የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል የፈፀመ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ሊጠየቅ አይገባውም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 14498 ሀምሌ 23 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን በመተላለፍ ሟች ይታይሽ አለማየሁ፣ አለባቸው መኩሪያውና ፋሲካ መኩሪያውን በቸልተኝነት የገደለ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡ ለዚህ ጥፋቱም ከፍተኛው ፍርድ ቤት በወሰነው መሠረት በሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና በአንድ ሺህ አምስት መቶ ብር መቀጮ ይቀጣል ብለናል፡፡
   ይህንን ቅጣት ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ ለክልሉ ፖሊስ ኮሚሽንና ለክልሉ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪ አመልካች በራሱ ይቻል ብለናል፡፡
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ

ነ/ዓ